# በሰላማዊ ትግል ሥም ውኸንብር

ባገራችን ኢትዮጵያ ቁጥራቸው እጅግ ከፍ ያለ የተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች እንዳሉ ይታወቃል ፤ እነዚህ ቁጥራቸው ወደ 90 የሚደርሱ የተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ሁሎቹም የሰላማዊ ትግል እንደሚያራምዱም ይናገራሉ : እነዚህ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች እያንዳንዳቸው ምን ያህል ደጋፊ እንዳላቸው በውል ባይታወቅም ከነዚህ በርካታ ተቃዋሚዎች ውስጥ ግን ቁጥራቸው ከ4 እና ከ 5 የማይበልጡ እንደ መኢአድ ፣ ኢዴፓ መድህን ፣ አንድነት ወይም አሁን ከሌሎች ጋር በመጣመር መድረክ በመባል የሚታወቁት ይገኙበታል ።

እንግዲህ ከላይ የዘረዘርኳቸው የተቃዋሚው የፖለቲካ ቡድኖች በሙሉ አሁን በስልጣን ላይ ያለውን የጎጠኛው ወያኔን አገዛዝ እንደሚቃወሙና ይህንንም ፀረ ህዝብና ፀረ ሀገር የሆነውን ወያኔን ቆርጠው ለመታገል እንደተነሱ ያውጃሉ ፣ በመሰረቱ የዲሞክራሲ ጭላንጭል በማይታይበት አገር ምን አይነት ሰላማዊ ትግል ማካሄድ እንደሚቻል ለኔ ግልፅ አይደለም ፣ ሆኖም ይህንንም ስል እነሱ የሚያራምዱትን ከመቃወም አንፃር ሳይሆን የወያኔን ባህሪ በመገንዘብ ነው ። እንደኔ እምነት ወያኔን ከስልጣን ማስወገድ የሚቻለው በአመፅና እምቢኝ አልገዛም ብሎ በመነሳት ነው ብዬ አምናለሁ ።

ወደ ተነሳሁበት ቁም ነገር ልመለስና አሁን ባገራችን ያሉ የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ፓርላማ ውስጥ ያሉም ሆነ ገና ወደፓርላማው ለመግባት በዝግጅት ላይ ያሉትንም ጨምሮ በእውነት እስከ ዛሬ ድረስ እነሱ እንደሚሉት የሰላማዊ ትግል ሲያራምዱ ነበርን? የሚለውን በኔ እይታ የተገነዘብኩትንና የተረዳሁትን ለማቅረብ እወዳለሁ ።

ሁላችንም እንደምናውቀው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲቋቋሙ ሁሉም ያገርንና የህዝብን ጥቅም አስጠባቂ እንደሆኑና ሆኖም ግን አንዱ ካንዱ የተሻለ አሰራርና አስተሳሰብ እንዳለው ለህዝብና ለሀገር ከሌላኛው የበለጠ እንደሚሰራና ቢመረጥም አገሪቱንም ሆነ ህዝቡን ወደ ተሻለ ጎዳና ሊመራና ሊያራምድ እንደሚችል በህዝብ መሀከል እየተዘዋወረ የህዝቡን ድጋፍና ተአመኔታ ለማግኘት ነው ። ነገር ግን ይህ በኛ አገር የሞሞከርም አይደለም ይህንን አይነት አካሄድ ለመሄድ የሚችለው አሁን በስልጣን ላይ ያለው አምባገነኑ አገዛዝ እንጂ ሌሎች ይህንን ለማድረግ አይችሉም ሊያደርጉም ቢነሱ መመሪያ ፣ ማድረግና ማድረግ የሌለባቸው ከአገዛዙ ተሰጥቷቸው በተወሰነላቸው ገደብ ብቻ ይሆናል ማለት ነው ። ይህ ደግሞ ሰላማዊ ትግል የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ከመሰረቱ ጀምሮ የሚፃረር ይሆናል ስለሆነም ባገራችን እየተካሄደ ያለው የሰላማዊ ትግል ሳይሆን ያጃቢነትና የሌለን ትግል እንዳለ የማስመሰል ግርግር ይሆናል ማለት ነው ።

በመሰረቱ ሰላማዊ ትግል ስንል ምን ማለታችን ነው? ይህንን ጥያቄ በአግባቡ ካልመለስን ዛሬ እነዚህ የተቃዋሚው ቡድኖች እያካሄዱ ያሉት ትግል ሰላማዊ ትግል ነው ወይንም አይደለም ብሎ ለመናገር ያዳግታል ። ስለሆነም እኔ እስከገባኝና እስከማውቀው ድረስ ሰላማዊ ትግል ምንና ምንን ያካትታል? የሚለውን በአጭሩ ለማስረዳት እሞክራለሁ ። በመሰረቱ ሰላማዊ ትግል ማለት መሳሪያ አንስቶ ከመፋለም በመለስ ያሉትን ሁሉንም አይነት የትግል አይነቶች ይጠቀልላል ብዬ አምናለሁ ፤ ስለሆነም በሰላማዊ ትግል ለጊዜው በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ እያራመደ ያለውን የውስጥም ይሁን የውጭ ግንኙነቶችን ከቅርብ ሆኖ በመመርመር በማይስማሙባቸው ነጥቦች ላይ ፣ ለሀገርና ለህዝብ አይበጁም ብለው በሚያምኑበት የውስጥም አሰራር ይሁን የውጭ ስምምነቶች ላይ ሁሉ ቅሬታን አለገደብ ለህዝብ በማሰማት አስፈላጊም ሆኖ ከተገኘ ቅሬታንና አለመስማማትን ለማሳየት ህዝብን ለተቃውሞ ለሰልፍ እንዲወጣ ፣ ወይንም የቅሬታና የአለመስማማት ምልክት የሆኑትን የስራ ማቆም አድማን መጥራት ፣ የርሃብ አድማን ማድረግና የመሳሰሉትን ያካትታል ። ታዲያ ዛሬ በአገራችን ስልጣን ይዞ ያለው የጎጠኞች አገዛዝ እያራመደ ያለው የውስጥ አስተዳደርም ይሁን የውጭ ግንኙነቶች አገር አፍራሽ መሆኑ እየታወቀ በአንዳቸውም የተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ጉዳዩ ሲነሳና ሲተችበት ፣ ወይንም ጉዳዩን በተመለከተ ህዝብን ሲያነቃቁና ሲያነሳሱ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅ ። ታዲያ እነዚህ የተቃዋሚ ቡድኖች ማንን ነው የሚቃወሙት? ወይንስ ሁሌም እንደምንሰማው እና እንደምንታዘበው የተቃዋሚው ተቃዋሚ ሆነው ነው እያገለገሉ ያሉት? ብለን እራስን እንድንጠይቅ ያስገድደናል ።

የወያኔ አገዛዝ እስከዛሬ በዓለማችን ላይ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ የማይታወቅ ባይነቱና በግብሩ እስካሁን ከምናውቃቸው የአምባ ገነን መንግሥታት ሁሉ በአይነቱም ይሁን በተግባሩ ለየት ያለ ነው ። አምባ ገነኖች በተፈጥሯቸው ጨካኝ ፣ ፍርደገምድል ፣ ለህዝብ ከበሬታ የሌላቸው ፣ በማሰር ፣ በመግደል የሚያምኑ ቢሆኑም ቅሉ ፤ ነገር ግን የአገራቸውን ዳር ድንበር በተመለከተ ፣ እንኳን ድንበራቸውን ቆራርሰው ለየጎረቤት ሀገሩ እንደ ቡና ቁርስ ሊያቀርቡ ይቅርና እንዲያውም በተቃራኒው የነሱ ያልሆነውን የጎረቤት አገር ክልል በመጣስ የይገባኛል ጥያቄ በማንሳት የወረራ ተግባር ሲፈጽሙ ነው የምናውቀው ። አይ የለም እንደ ወያኔም አገር ቆርሰው ይሰጣሉ የሚል ካለ ከዚህ ቀደም ሰምቼም አንብቤም ስለማላውቅ አለ የሚል ካለ ቢያመላክተኝ እወዳለሁ ። ታዲያ የኛ የሰላም ታጋዮች ይህንን ተግባር እያዩና እየሰሙ አይቶ እንዳላየ ፣ ሰምቶ እንዳልሰማ መሄዱን መርጠዋል ፤ ይህንን አገር ቆርሶ ለባእዳን መንግስት መስጠትን በተመለከተ ደጋፊዎቻቸውን አሳውቀው ህዝብ ለተቃውሞ እንዲወጣ መጥራት ካልቻሉ ተግባራቸው ታዲያ ምንድነው? ወያኔን እሹሩሩ እያሉ በየምርጫው እያጀቡ የይስሙላ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ለማስመሰል ነው? ወይንስ ፍርሃት? ፍርሃት ከሆነ ደግሞ እየፈሩ መታገል የሚባል ነገር አይገባኝም ፤ የፈራ አርፎ ቤቱን ዘግቶ አፉን ለጉሞ የሚነገረውንና አድርግ የሚባለውን እያደረገ እንደ እንስሳ የሚኖር ጨርቅ በመልበሱ ብቻ ከእንስሳ የሚለይ ፍጥረት ብቻ ነው ።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ዛሬ በስልጣን ላይ ያለውን የወያኔ አገዛዝ የሚያጋልጡበትና ህዝብን ለአመፅ ሊያነሳሱበት ከሚችሉት አያሌ አገራዊና ህዝባዊ ጥያቄዎች መካከል በአበይትነት ሊጠቀሱና ወያኔንም ማንገዳገድ ብቻ ሳይሆን ከስሩ መንግለው ሊጥሉ ከሚችሉ ጠንካራ ነጥቦች ውስጥ በዋነኛነት የሚጠቀሱት ፤ በቅርቡ ለሱዳን መንግስት የሰጠው ሰፊና ለም መሬት በአበይትነት ሊጠቀስ ይችላል ። ይህም መሬት

ከሰሜን ጎንደር እስከ ደቡብ ጋምቤላ የሚደርስ ሲሆን እርዝመቱም 1600 ኪሎሜትር ፤ ጥልቀቱ ከ 30 እስከ 60 ኪሎሜትር የሚደርስ እንደሆነ ይታወቃል ፤ ሌላው ለሳውዲ አረቢያ ፤ ለህንድ ፣ ለቻይና ፣ ለኢንዶኔዢያ ፣ ለኮሪያና ለመሳሰሉት አገሮች እጅግ በጣም ለምና ሰፊ የእርሻ መሬቶችን ገበሬውን እያፈናቀሉ ለባእዳን መሸጡ ፣ በእድሜያቸው እጅግ ለጋ ወጣት የሆኑና ህፃናት ሴቶችን ለአረብ ኤመረትና ለመሳሰሉ አገሮች ለባርነት መሸጥ ፣ ህፃናትን ከናታቸው ጉያ እያፈኑ ወላጅ አልባ ናቸው በማለት በማደጎ ስም ሰፊ ኢሰባዊ የሆነ የዜጋ ሽያጭ በገዢው የአፈና ቡድን እየተራመደ ባለበት አገር ፤ ህዝብን ለአመጽና ለእንቢተኝነት መጥራት የማይችል ተቃዋሚ ቡድን ተቃውሞው ምን ላይ እንደሆነ ለመረዳት ያዳግተኛል ።

እንደ እውነቱ ከሆነ እነዚህ እራሳቸውን በተቃዋሚነት የሚጠሩት ቡድኖች የወያኔ መሳሪያ ፤ ህዝብ ማደናገሪያ እየሆኑ ነው  የመጡት እንጂ ለሀገርና ለወገን የሚበጅ አንድም ይሄ ነው ተብሎ የሚጠቀስ አመርቂ ድርጊት እስካሁን ፈጽመው አላየሁም ። እንደሚባለውም ታማኝ ተቃዋሚ ናቸው ። አዎ ታማኝ ! ታማኝነታቸውም ለህዝብና ላገር ሳይሆን ፣ ታማኝነታቸው ለወያኔ ነው ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም ። እኔ ባለሁበት አገር ሁለት ትልልቅ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ ሌሎችም እንዲሁ ብዙ ደጋፊና ተከታይ ባይኖራቸውም የተለያዩ ሁለትና ሶስት የሚደርሱ የፖለቲካ ቡድኖች አሉ ታዲያ ሁሎችም ታማኝ ተቃዋሚዎች ናቸው ። ታዲያ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ እንጂ ለጊዜው በስልጣን ላይ ላለው የፖለቲካ ቡድን አይደለም ። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ልዩነቱ ፣ ታማኝ ተቃዋሚ ማለት ታማኝነቱ የሚሆነው ላገሩ ፤ ለህዝቡና ፤ ለህገ መንግሥቱ እንጂ በስልጣን ላይ ላለው ቡድን አይደለም ። ሆኖም ግን ባገራችን ህገመንግሥቱ ወያኔ ፤ ወያኔም ህገመንግሥት በሆነበት አገር ታማኝነት ለህገ መንግስት ተባለ ወይንም ለወያኔ ለውጥ አይኖረውም "ስልቻን ቀንቀሎ ፣ ቀንቀሎን ስልቻ" ማለት ነው ። ዛሬ ባገራችን ያለውን ህገመንግሥት ወያኔ በአንድ አዳር የመለወጥ ፣ የመሰረዝ ፣ የመጨመር ፣ የመቀነስ ፣ እንዳሻው ለማድረግ ሙሉ መብቱን ይዞ የሚጓዝ አምባገነን ስርአት ነው ። ፓርላማውን እረግጦና አፍኖ ለይስሙላ ወያኔ  የሚደሰኩረውን ዲስኩር አድምጠውና አጨብጭበው ለመሄድ የተቀመጡ አሻንጉሊቶች እንጂ ለህዝብ የሚበጅ ሊያበረክቱ የሚችሉት አንድም ነገር የላቸውም ።

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነው የተቃዋሚ ቡድኖች ለህዝብና ላገር ቆመናል በማለት ወያኔን ለመቃወም ወያኔ ባመቻቸላቸው የይስሙላ የምርጫ መድረክ ለመሳተፍና ፓርላማ ገብተው ለሀገርና ለወገን ለውጥ ልናመጣ ነው የሚሉን ። እስቲ ማን ይሙት እስካሁን በተቃዋሚነት ፓርላማ ውስጥ ከተኮለኮሉት አስቂኝ ነገሮች ለኢትዮጵያ የሚበጅና የሚጠቅም አንድ ነገር ቀርቦ ተከራክረውበት ፣ አሸንፈው ስራ ላይ ውሎ ህዝብን ያመረቃ ተግባር መናገር ይቻላል? ለመሆኑ ፓርላማ ውስጥ ያሉት ወያኔ በምዕራባውያን ትዛዝ ጌቶቹን ለማስደሰት ብሎ ሱማሌ ውስጥ በጣልቃ ገብነት ገብቶ የምዕራባውያኑ ጥቅም አስጠባቂ በመሆን የተማገደበት ጦርነት ምን ያክል የሰው ህይወትና የንብረት ውድመት እንዳደረሰ ፣ እንዲሁም ጦርነቱ ምን ያክል ገንዘብ እንደፈጀ ፣ መጠየቅ ይችላሉ? ጠይቀውስ ያውቃሉ? ለጥያቄያቸው በአግባቡ መልስ አግኝተው ያውቃሉን? ታዲያ ይህንን ማድረግ የማይችል የፓርላማ ተመራጭ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግልጋሎቱ ምንድነው? ለሱዳንስ መንግሥት በጥቂት የወያኔ የአመራር አባላት መልካም ፈቃድ ብቻ ተቆርሶ የተሰጠው መሬታችን ለመሆኑ በፓርላማ ውስጥ ተነጋግረውበት ያውቃሉ? ጉዳዩን ሰምተው እንዳልሰማ አይደለም ያለፉት? ለየአረቡና ለህንዱ የሚቸበቸበው መሬትስ ጉዳይ? ፓርላማው ደጅ ደርሶ ይሆን? እነዚህንና የመሳሰሉትን አንኳር የሆኑ ህዝብን የመቀስቀሻና የማነሳሻ ጉዳዮችን ማንሳት ካልቻሉ ታዲያ ፓርላማ ውስጥ የደደቢት መፍለሶች ሲቀድሱ አድምጦ የሰማነውን በልቦናችን አሳድርልን ብሎ መውጣት ይሆን ትግል ማለት? ያ ከሆነ በትግል ስም ታላቅ ቀልድ እየተካሄደ ነው ማለት ነው ። የሰላማዊ ትግል የሚለውም ቃል ባለቤት ቢኖረው አላግባብ ስሜን አጠፉት ብሎ ከመክሰስ ወደኋላ እንደማይል መገመት አያዳግትም ።

ኢትዮጵያ ውስጥ የኑሮ ውድነት ፣ የስራ አጥነት ፣ የትምህርት አሰጣጥ አድሎ ፣ የግንባታ አድሎ ፣ የአንድ ብሄር ገናናነት የበላይነትና ሁሉን ነገር የመቆጣጠር ሁኔታ ፤ ይህ ሁሉ በሀገራችን ውስጥ እየታየ አይደለም ማለት ይሆን? አለ ከተባለስ እነዚህ ሁኔታዎችና ከላይ የጠቀስኳቸው አንኳር የሀገርና የህዝብ ጉዳዮች ህዝብን ለማነሳሳት ካልበጁ ከነዚህ ነጥቦች የበለጠ ህዝብን ሊያነሳሱ የሚችሉ ጉዳዮች ምንና ምን ሊሆኑ ነው? በነዚህ ነጥቦችስ ላይ ተመርኩዘው ወያኔን ለማስወገድ መስራት ካልቻሉ ምን የተቃውሞ ሀሳብ ይዘው ሊሰሩ ይሆን? በምርጫ ግርግር የሚያደናቁሩን ?

ሰሞኑንም አራት የተለያዩ የተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች የገዢውን የወያኔን ቡድን ጨምሮ ማለት ነው ፣ መጪውን የ 2002ን ምርጫ አስመልክቶ የስነምግባር ስምምነት መፈራረማቸውን እየተፍነከነኩ ወያኔን አንበረከክነው በማለት ሊነግሩን ሲዳዳቸው አስተውለናል ፤ ለመሆኑ ማ ማንን ይሆን ያንበረከከው? መልሱን ለራሳቸው ህሊናቸውን እንዲጠይቁ እተውላቸዋለሁ ፤ አፍ ቢዘላብድም ፣ ህሊና ግን አይዋሽምና ። ድርድሩ ወይንም ስምምነቱ ገና ከመሰረቱ የተበላሸና ተልካሻ ነው ። ይህንንም የምልበት አንደኛውና ዋነኛው ምክንያት ወያኔ ጠሪ ሌላው ተጠሪ ሆነው ነውና የቀረቡት ፤ ይህ ብቻ ሳይሆን ወያኔ የጉዳዩ የበላይ አካል በመሆን እሱ እንደሚፈልገውና እሱ በውጪው ዓለም ያለውን አስቀያሚ ገጽታ አንበረጭቃ ቀባብተው አመዳም ፊቱን ወዛም እንዲያስመስሉለት የተጋበዙ ሳይሆኑ የተጠሩ አዳማቂ ቡድኖች ናቸው ። በስምምነታቸውም ላይ አንድም የወያኔን መጥፎ ገጽታ ለህዝብ እናሳውቃለን ብለው ቢነሱ ስምምነቱ ጥሳችኋል በመባል ከምርጫው መውጣት ብቻ ሳይሆን ሊያሳስራቸው ፣ ካገር ሊያሰድዳቸው ብሎም ሊያስገድላቸው የሚችል የወያኔ የማነቂያ ሸምቀቆ ውስጥ ሳይገደዱ ወደው የገቡበት ነው ።

የ2002 ቱን ምርጫ በተመለከተ ከወያኔ ጋር ሊወዳደሩና ወያኔን ሊወነጅሉ የሚችሉት ወያኔን ሊጎዳ በማይችልና ነገር ግን ላላዋቂ እውነትም በድፍረትና በቁርጠኝነት ወያኔን የሚሞግቱት መስሎ ለመቅረብ የተመቻቸ እዚህ ግባ የማይባል የተቃውሞ መፈክር በማንሳት ይሆናል ። ይኸውም ፤ ወያኔ ለሀገርና ለህዝብ አይበጅም ፣ ወያኔ ስራ አጥነትን ፣ እረሃብን ፣  ድንቁርናን አልተዋጋም ፤ እኛን ግን ብትመርጡን እነዚህን ሁሉ እንፈጽማለን ወዘተ ... የመሳሰሉ ሰንካላ ነጥቦችን እንጂ ከትምህርቱ ፣ ከርሃቡ ፣ ከስራ ጥነቱ ፣ ከኑሮ ውድነቱ ባሻገር ወያኔ አገርህን

ለሱዳን ሸጦታል ፤ መሃል አገሩን ደግሞ ለህንድና ለአረብ እንዲሁም ለቻይና እየሸጠው ነው ፤ ህፃናት ልጆችህን ከወላጆቻቸው እያፈነ በማደጎ ስም ወደ ውጪ በዶላር እየቸበቸባቸው ነው ፤ ወጣት ልጃገረዶችንም ለየ አረብ አገሩ ግርድናና ባርነት ፣ እንዲሁም ለወሲብ ማርኪያ እንዲሆኑ በዶላርና በዩሮ እየመነዘራቸው ነው ብለው ህዝቡ እነሱን እንዲመርጥና ከነናቸው እንዲሰለፍ ማድረግ አይችሉም ። ይህንን ካደረጉ ባንገታቸው ተገደው ሳይሆን ወደው ያጠለቁትን ገመድ ወያኔ ሸምቀቆውን እንዲያጠብቅ መጋበዝ እነደሆነ ያውቁታል ፤ ከወያኔም ጋር የተማማሉት እነዚህን ቁስሎቹን ላይነካኩበት ነው ። "ውሸን ያነሳ ውሻ ይሁን" ተባብለው ነው የተለያዩት ። ታዲያ እኛ አይናችሁን ጨፍኑና እናሞኛችሁ ሲሉን እሺ ብለን ልንቀበል ይፈልጋሉን? ያ በኔ በኩል የማይሞከር ነው በብዙሀኑም ኢትዮጵያዊ እንደዚያው ይመስለኛል ።

ለነገሩ "ሲሉ ሰምታ" ሆኖ ነው እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም አይነት የሰላማዊ ትግል እየተካሄደ አይደለም ፣ እየተካሄደ ያለው ወያኔ ሰራሽ የይስሙላ ትግል ነው ። ወያኔ ሙሽራ ሆኖ ሌሎቹ አጃቢና አጨብጫቢ በመሆን አፍ ላይ ደም ደም የሚልና የሚኮመዝዝ የሽቃጭ ትያትር እየተሰራ ነው ። እንዲያውም ይህ የወያኔና የሌሎች አዳማቂዎች ግርግር እንደተፈራረሙ ከጥቂት ቀናት በኋላ አንዱ የድርጅት መሪ ተብዬ ስለ ምርጫ ኮሚሽኑ ሲጠየቁ ፤ የምርጫ ኮሚሽኑ እኛ ወደዚህ ወደ ድርድሩ ከመምጣታችን በፊት በሌሎች የተወሰነና ያለቀለት ጉዳይ ስለሆነ ስለምርጫ ኮሚሽኑ ምንም ማድረግ አይቻልም በማለት በአንድ የሬድዮ ጣቢያ ቀርበው አስደምመውን አልፈዋል ። የምርጫ ኮሚሽኑም ቀደም ብሎ የተቋቋመ መሆኑን ሲነግሩን "ተደራደርን አንበረከክነው" ከሚሉት በተፃረረ መልኩ በመሆን የምርጫ ኮሚሽኑ አፈ ቀላጤ የሆኑት ዶ/ር ተብዬ እንዲህ ሲሉ በአንድ ወያኔ አፍቃሪ ድረገጽ ላይ አስነብበውናል "ዶ/ር አዲሱ፡- በእኛ በኩል፣ ቦርዱ ምንም ችግር የለውም፡፡ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅት እያደረግን እንገኛለን፡፡ ስለዚህም የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በየጊዜው ይፋ እያደረጋቸው ያሉ ሥራዎች እራሱ ገላጭ ነው፡፡ ህጉን ተንተርሰን ወደ 16 የሚሆኑት ደንቦችና መመሪያዎችን አዘጋጅተን ከሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ትውውቅ እንዲያደርጉ አድርገናል፡፡ ሌላው፣ የዛሬ አንድ ዓመት ገደማ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥሪ አድርገን፣ በኢሲኤ አዳራሽ በተለያየ ጊዜ ስልጠናዎች እየሰጠን ቆይተናል፡፡ የክልል ጽ/ቤቶችን አስፈፃሚዎች በመቅጠር አስፈላጊውን የጽ/ቤቶችን የማደራጀት ሥራ እየሰራን፣ አሁን ሥራቸውን ክፍት አድርገው የሚጠብቁበት ደረጃ ደርሰናል፡፡ በየቦታው ያሉትን የምርጫ አስፈፃሚዎችን መልምለናል፡፡ የተጓደሉትንም ተክተናል፡፡ የጽ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የቦርድ ስትራቴጂ እቅድ አፅድቀናል፡፡ የሚያስፈልገውን ለምርጫ ባጀት ሁሉ ከገንዘብ ሚኒስትር አስፈቅደናል፡፡ ለምርጫ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ሁሉ አዘጋጅተናል፡፡ የመራጮች ካርድ፣ የዕጩዎች ካርድ፣ ኮሮጆ፣ ሰነዶች በሙሉ ተዘጋጅተው ታሽገው ለምርጫ ዝግጁ አድርገናል፡፡ የምርጫ ጊዜ ሰሌዳም ቦርዱ አይቶ የፖለቲካ ፓርቲዎች አወያይቶ፣ ጊዜው ይራዘምልን ብለው ባቀረቡት ጥያቄ መሠረት ይፋ አድርገናል፡፡ እንግዲህ ይሄ ሁሉ ሥራ ለምርጫ 2002 የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ናቸው፡፡ በሚቀጥለው ደግሞ ለምርጫ አስፈፃሚዎች ስልጠና የምንሰጥበት ጊዜ ደርሷል፡፡ ለጋዜጠኞቹ፣ ለፖሊስ፣ ለዳኞች የሚሰጠው ስልጠና ደግሞ መርሀ ግብር ወጥቶለት ጽ/ቤቱ አስፈላጊው የበጀት ድልድል እያደረገ ይገኛል፡፡ ሌላው በጊዜው ሰሌዳ መሠረት ፓርቲዎች ቅስቀሳ ያደርጋሉ፡፡ ዜጎች ወጥተው እንዲመርጡ ወጥ የሆነ የስነ ዜጋ ትምህርት (ማንዋል) ተዘጋጅቷል፡፡ በቅርቡ ለሕዝቡ እንዲደርስ እናደርጋለን፡፡"

ለመሆኑ ዋናውና ልንታገለው ብሎም በገለልተኝነት ሊቋቋውም ይገባል የምንለው የምርጫ ኮሚሽኑ አልነበረምን ? ምርጫ ኮሚሽኑ አይደለም እንዴ ያለፈው የ 97 ቱን ምርጫ ከወያኔ ጋር በማበር ሲያጭበረብርና ሲያዘርፍ የነበረው? ዛሬ ኮሚሽኑ ባባ ዲያቢሎስ ተባርኮ ንስሀ ገብቶ ክንፍ ሊያወጣ እያቆጠቆጠ ያለ የባህታውያኖች ጥርቅም ስለሆነ ነው ምርጫ ኮሚሽኑን መንካት የተፈራው? ለነገሩ ከላይ እንደጠቀስኩት እየፈሩ ትግል ስለሆነ አካሄዱ ሁሉ ሽፋፋና ወልጋዳ ቢሆን ለኔ አይደንቀኝም ፤ እንዲያው ትንሽ ሁኔታው ግር ያለው ካለ ሁኔታውን ግልፅ ለማድረግ እንጂ ። ምነው በዚህ ድርድራቸው ላይ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ ብለው አልጠየቁም? ወያኔን አንበረከክነው ካሉን ዘንዳ ፤ ይቅርታ ! ለካስ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ጠይቀናል ብለዋል ድንቄም አሉ! ታዲያ ድርድሩ ከመፈረሙ በፊት አልነበረም እንዴ መልካም ፈቃድን ለማሳየት የፖለቲካ እስረኞች መፈታት የነበረባቸው? ወይስ ከምርጫው በኋላ ነው ሊፈታላቸው የተስማሙት? ለነገሩ ይህንን መሳለቂያ በነገሩን በማግስቱ የወያኔው ቁንጮ አማካሪ የሆነ በማግስቱ ወጥቶ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድም የፖለቲካ እስረኛ የለም ብሎ ሊያስቀን ሞክሮ አልፏል ። ታዲያ ወያኔ የፖለቲካ እስረኛ የለም እያለን እነሱ የትኛውን የፖለቲካ እስረኛ ሊያስፈቱልን ይሆን የተማማሉት? ወይስ "ሺ ዝንብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም" ብለን አዝነንባቸው ፣ ታዝበናቸው እንድንበተን ይሆን?

በሰለጠነው አለም ፣ ወይንም እኔ ባለሁበት አገር ዛሬ በስልጣን ላይ ያለው የዲሞክራቱ ፓርቲ ነው ፤ የዲሞክራቱ ፓርቲ የሪፓብሊካኑን ፓርቲ በሚቀጥለው ምርጫ ምን ማድረግ እንዳለበት ፣ ምን ማድረግ እንደሌለበት ፣ መመሪያ ሊሰጠው አይችልም አይዳዳውምም ። ምንም ለጊዜው ስልጣን ላይ ያለው ዲሞክራቱ ቢሆንም ሁለቱም ከህገመንግሥቱ ስር ሆነው ህገመንግሥቱን አክብረው በዚያ መሰረት ይንቀሳቀሳሉ እንጂ አንዱ አንዱን ሊመራ ወይንም መመሪያ ሊሰጥ አይችልም ። ባለፈውም ከአንድ አመት በፊት የሪፓብሊካኑ ቡድን ስልጣን ላይ በነበረበት ወቅትም ዴሞክራቶችን ማድረግ የምትችሉትና የማትችሉት ብሎ መመሪያ እንዳልሰጠ ሁሉ ፤ ነገር ግን እኛ አገር ሲደርስ ወግ ወጉ ይያዝና ዲሞክራሲ ባናቷ ትቆማለች ። መጀመሪያ ወያኔን ማስደሰት የፓርቲዎች ሁሉ ተቀዳሚ መርሆ ሆኖ በማስከተልም እርስዎ እንዳሉ እኛ ህፃናት ልጆች ስለሆንን ማድረግ ያለብንንና የሌለብንን ይንገሩን በዚያ መሰረት ልናገለግል ፈቃደኞች ነን ከማለት በቀር ምንም እንደ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድን ሲሰሩም ሆነ ሲንቀሳቀሱ አይስተዋልም ። ወያኔ እውን ለዲሞክራሲ ተገዥ ቢሆን መጀመሪያ ለህዝብም ሆነ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች መልካም ምኞት እንዳለው ለማሳየት የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞችን መፍታት ነበረበት በሁለተኛ ደረጃ እሱ አደራዳሪ እሱ አቀራራቢ ሳይሆን እሱም ከሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች እኩል እንጂ ብልጫ እንደሌለው በመገንዘብ በእኩልነት መንፈስ ወደ ድርድር መምጣት አሊያም ከሁሉም የፖለቲካ ቡድኖች ነፃና ገለልተኛ የሆነ ቡድን እንዲያደራድራቸው ማድረግ ፤ ነጻና ገለልተኛ አደራዳሪ ቡድኑም አገራዊና አገር በቀል እንጂ የተደራዳሪውን ጭንቅላት በኩርኩም እየነደለ እሺ ጌታዬ የሚያሰኝ የውጭ ኃይል መሆን አይኖርበትም ። ለተቃዋሚውም እኩል የነጻ ጋዜጣ ፣ የሬድዮና የቴሌቭዥን ጊዜ መስጠት ። የታገቱ የሚዲያዎች ግልጋሎት እንዲሰጡ መፍቀድ ፣ ህዝብ የማወቅ መብት ስላለው ከውጭም ይሁን ከውስጥ የሚተላለፉ የሬዲዮ የቴሌቭኢዥንና ድረገጾችን መክፈት ይጠበቅበታል ። ይህ ሳይሆን ወያኔ መልካም ምኞት እያሳየ

ነው ብሎ መናገር የወያኔን ተፈጥሯዊ ባህሪ አለማወቅ ፣ ካልሆነም ሆዳደርነት ፣ ፍራቻና የመሳሰሉትን ከመሆን አያልፍም ። ይህ ሲሆን ብቻ ነው ወያኔ ለዲሞክራሲና ለሰላም መልካም ፍላጎት እያሳየ ነው ልንል የምንችለው ፤ እነዚህ በሌሉበት ስፍራ በእመኑኝና እንተማመን አገርን ላጥፊዎች አሳልፎ መስጠት ከተጠያቂነት አያድንም ።

አንዳንዶች እናንተ እውጪ ተቀምጣችሁ የማይፈጃችሁን እሳት አታቀጣጥሉ ሲሉ ይደመጣሉ ፤ ላላዋቂ አባባሉ ትክክል ሊመስል ይችላል ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ላንዱ እናት ለሌላው የንጀራ እናት አይደለችም ፤ ዲሞክራሲንና መብትን በተመለከተ እንድ በረንዳ አዳሪ ያጣ የነጣ ደሃና የወያኔው ቁንጮና መሰሎቹ እኩል ናቸው አንዱ ካንዱ አይበልጥም፣ አያንስም ፤ ስለሆነም አንድ ግለሰብ ካገሩ ውጪ ስለሆነ ስለሀገሩ መተቸት ፣ የሚያምንበትን አስተያየት ከማቅረብ ፣ ያልፈለገውን ከመቃወም ፣ የሚያግደው አንዳችም ነገር የለም ። የፖለቲካ ቡድኖችም የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል እስካሉና ህዝብን እንወክላለን እስካሉ ድረስ ፣ ህዝብ ከአገር ውጪ ያለም ይሁን አገር ቤት ውስጥ ያለም በእኩል ሊተቹ ፣ ሊነቅፉ፣ ሊደግፉ እንደሚችሉ ማወቅ የግድ ይላል ። ያ እንወክለዋለን ወይንም መከራውና ግፉ መከራና ግፋችን ነው የሚሉት ህዝብ ያለው ውስጥም ውጪም ነውና ፤ አንድን የፖለቲካ ቡድንም ለመደገፍም ይሁን ለመውቅስ የግድ የተባለው ድርጅት አባል ወይንም ደጋፊ መሆን አይጠይቅም ፤ እንዲያማ ከተባለ ወያኔንም ለመተቸትና ለመውቀስ ወያኔ ካልተሆነ አይቻልም ሊባል ነው ማለት ነው ። ስለሆነም እንታገላለን ከተባለ ሊያመጣ የሚችለውን ጣጣ ሁሉ ገምቶና አውቆ እንጂ ሊያሳስረኝማ ከሆነ ፤ ሊያስገድለኝማ ከሆነ እየተባለ ትግል ፣ ትግል አይደለም ። ያንን የሚሉ ከሆነ ከትግሉ ጎራ ገለል ማለት ነው ። ልጅን "ሲወዱ ከነፍጡ" ይባል የለ ፤ አሊያ ለህዝብ ቆመናል እንታገላለን እያሉ ሞትና እስራትን መሸሽ አይቻልም ።

የህዝብን ብሶት ባግባቡ ማሰማትና ማስተናገድ ካልተቻለ የህዝብን ጥያቄ እያድበሰበሱ የህዝብን ሰቆቃ በእጅ መንሻነት ማቅረቡ ይቁም ። ለውጥ እንደሆነ እነዚህ <u>ለይስሙላ የተደረደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች</u> ኖሩም አልኖሩም መምጣቱ አይቀርም ፤ በርግጥ ከልባቸው ላገራቸውና ለወገናቸው በድፍረት ለመታገል የተነሱ ቢሆን ኑሮ ለውጡ ሊፋጠን ይችላል ። እንዲዚያ ካልሆነ ግን ህዝብን ከማዘናጋት በቀር የሚፈይዱት አንዳችም ፋይዳ ይኖራል ብዬ ለመገመት ያዳግተኛል ። አሁንም እነሱ ኖሩም አልኖሩም ለውጥ መምጣቱ አይቀርም ፤ በአፄ ኃይለስላሴ ዘመን ለውጥ ሲመጣ እንደዛሬው 90 የፖለቲካ ፓርቲ ሳይሆን አንድም የፖለቲካ ፓርቲ እንዳልነበረ እናውቃለን ፤ ህዝብ በቃኝ ሲል ፓርቲ ኖረ አልኖረ ሕዝብን ከፍላጎቱ ሊገታው የሚችል አንድም ኃይል ሊኖር እንደማይችል ከራሳችን የታሪክ ሂደት መማር ይኖርብናል ። ነገር ግን የዚያን ጊዜው የህዝብ እምቢተኝነት ለውጥ ቢያመጣም የተደራጀ ኃይል ባለመኖሩ የህዝብ ድል በአምባ ገነን የጦር መኮንኖች ሊቀማ ችሏል ። አሁንም የተቃዋሚ ቡድኖች ህዝብን ማቀፍና በህዝብ ፍላጎት ላይ ተመርኩዘው መንቀሳቀስ ካልቻሉ እራሱ ህዝብ ያለፈውን ታሪኩን ይደግማል ሆኖም ግን አሁንም የስልጣኑ ባለቤት እሱ ይሆናል ለማለትና አስቀድሞ ለመተንበይ ግን አቅሙ ባይኖረኝም ሊሆን ይችላል የምለው የራሴ ግንዛቤ ግን ይኖረኛል ። ስለሆነም ደግሜ ደጋግሜ ለማሳሰብ የምሞክረው ባገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ የሰላማዊ ትግል እየተካሄደ እንዳልሆነና እንዲያውም ወያኔን የሚጠቅም የማደናገሪያና የማደናቆሪያ ትግል ግን እየተካሄደ እንደሆነ ለማሳሰብ ነው ። እየፈሩ ትግል ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም ፤ የፈራ አርፎ ቤቱ ይቀመጥ ፣ አፉን ይለጉም ፣ በዲያስፖራ የሚገኘውም ኢትዮጵያዊ ታጋይ አገር ቤት እናት ፣ አባት ፣ ወንድም ፣ እህት ፣ ልጅ ፣ አክስት ፣ አጎት የሌለው ይመስል የማይፈጃችሁን እሳት አታቀጣጥሉ የሚለውን ስፍራ ሳይሰጡ የሚፈጀውን እሳት እያቀጣጠለ መሆኑን በማስረገጥ ለሚደርስበት ሰንካላ ትችት ቁብ ሳይሰጥ ትግሉን በቆራጥነት እንዲቀጥል ሳላሳስብ አላልፍም ፤ አሁንም የህዝብ ድል ፓርቲዎች ኖሩም አልኖሩም መምጣቱ አይቀርም ይዘገያል እንጂ ።

ድል ለምዝብሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ

ውድመት ለወያኔ

አይምሮ ዳኛቸው